በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
NATIONAL LOTTERY ADMINISTRATION

**815/2013**

ቁጥር / No 503/ገለ/2005
ቀን / Date 15/2/2005

***ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር***
***አዲስ አበባ፣***

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 21 መሠረት ባለሥልጣኑ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ የአፈፃፀም መመሪያዎችን ለማውጣት እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ መመሪያ እና የህገወጥ ሎተሪ ስራዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ አዲስ እንደዚሁም የፕሮሞሽን ውድድር ስራዎች የፍቃድ አሠጣጥና ቁጥጥር እና የቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ማሻሻያ መመሪያዎች በባለሥልጣኑ ጸድቀው እንዲወጡ የመመሪያዎቹን የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ አቅርበን በመመሪያዎቹ ላይ ከባለሥልጣኑ የበላይ አመራሮች ጋር ባደረግነው የጋራ ውይይት መስተካከል፣መታረም፣መሻሻል በሚኖርባቸው አንቀጾች ላይ አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ የመመሪያዎቹን ረቂቅ አዘጋጅተናል፡፡

ስለሆነም መመሪያዎቹ እንዲጸድቁልን የመመሪያዎቹን ረቂቅ ኮፒ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ያቀረብን መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገረመው ጋርጂ
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፣
- ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለፈቃድ አሠጣጥና ቁጥጥር የስራ ሂደት
  ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር
  አዲስ አበባ፣

ስልክ +251-111569069 TEL. +251-111550144/45 | ፖ.ሣ.ቁ 274 POBOX | ፋክስ +251-111552511 FAX +251- 111569197 | Email lgm@telecom.net.et gergarj2@yahoo.com Website www.nla.gov.et | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ADDIS ABABA-ETHIOPIA

# የፕሮሞሽን ውድድር ሥራዎች

## የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ

## መመሪያ

## ቁጥር 815/2013

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# የፕሮሞሽን ውድድር ሥራዎች
# የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 815/2013

ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ወይም አገልግሎቶቻቸውን በስፋት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በማስተዋወቅ የገበያ ማስፋፊያ ሥራ በመስራት ውጤታማ መሆን እንዲያስችላቸው የፕሮሞሽን ውድድር ማካሄድ ስለሚፈልጉ፣

የሚያከሄዱት የፕሮሞሽን ውድድር ዓላማው ምርታቸው/አገልግሎታቸው በስፋት ገበያ ውስጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ በመሆኑ በፕሮሞሽን ውድድሩ የሚሳተፈውን ህብረተሰብ መብት እንዲጠበቅ ማድረግና የመንግስትንም ግዴታዎች በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል፣

የፕሮሞሽን ውድድር ማካሄድ ዓላማው ምርትን/አገልግሎትን ለህብረተሰብ ለማስተዋወቅ በመሆኑ፣ ጤናማ ያልሆነ ውድድር በድርጅቶች መሃል እንዳይፈጠር መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ ድርሻ ኖሯቸው ተፈላጊ ውጤት ማለትም የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ለመጠበቅና ለማበረታታት፣

አስተዳደሩ ከተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 160/2001 እና በአስተዳደሩ በተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤት የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት እና በሥራውም ወቅቱ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ መጠቀም እንዲቻል ተደርጎ መመሪያ ቁጥር 42/2002 መሻሻል እንዳለበት በመታመኑ እና አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም የሎተሪ ሥራ ማካሄድ አይችልም በሚል በመደንገጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 21 መሠረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቶአል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሻሻለ የፕሮሞሽን ውድድር ሥራዎች የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 815/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡-

1. “ባለስልጣን እና ዋና ዳይሬክተር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የባለስልጣኑ መ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

2. “የፕሮሞሽን ውድድር” ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭን ለማሳደግ የሚካሄድ በዕድል ወይም በዕጣ ወይም ትንበያን ባካተተ የጥያቄ መልስ ውድድር መልክ፣የአጭር መልእክት አገልግሎትን በመጠቀም ወይም በማ ቸውም ሌላ መንገድ የሚከ ወን ሎተሪ ሎተሪ ነክ እንቅስቃሴ ሆ ፤ ከምርቱ መጠቅለያ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ወይም በምርቱ ክዳን ውስጥ ተደብቀው የሚገኙ ወይም ከምርቱ/ከሸቀጡ ወይም ከአገልግሎቱ ግዢ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚታደሉ ባለዕድል የሚያደርጉ ኩፖ ችን የሚፋቁ ካርዶችንም ይጨምራል፡፡

3. “ፈቃድ” ማለት ዕጣን ወይም ዕድልን ያካተተ ለሽያጭ ማስፋፊያነት የተለያዩ ሰዎች እንዲጠቀሙበት የሚሰጥ ዕድሳት የሌለው ፈቃዱ ለሚሰጥበት ለተወሰነ የጊዜ ክልል ብቻ የሚያገለግል የፕሮሞሽን ውድድር ፈቃድ ነው፡፡

4. “አስተዳደር” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው፡፡

5. “ሰው” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

3. <u>ፈቃድን በተመለከተ</u>

1. የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ ሁኔታ

ሀ. ማንኛውም ሰው የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅቶችን ለማካሄድ ሲፈልግ ለአስተዳደሩ በፅሁፍ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ. ፈቃድ ጠያቂው ሰው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

1. የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት ፈቃድ ጠያቂውን ድርጅት ስም ሙሉ አድራሻ፤
2. የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት ፈቃድ የሚጠይቅለትን ምርት/ሸቀጥ ወይም አገልግሎት አይነት ስም ለይቶ በመጥቀስ ምርቱ /ሸቀጡ ወይም አገልግሎቱ ከዝግጅቱ በፊት

የነበረውን  በዝግጅቱ ወቅት የሚ ረውን የመሸጫ ዋጋ፣ የሥርጭት ሽፋኑንና ቦታውን የሚያመለክት መረጃ፤

3. ከፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅቱ በፊት ባሉት ፕሮሞሽኑ ተግባራዊ ከሚሆንበት የጊዜ ክልል/ወሰን/ ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ወራት ውስጥ ፈቃድ የተጠየቀለት ምርት የሽያጭ መጠን/መለኪያ  ብዛት/ እ  ጠቅላላ ዋጋ፤

4. የፕሮሞሽን ወድድር ዝግጅቱ ሊካሄድ በታሰበበት የጊዜ ክልል/ወሰን/ ውስጥ ፈቃድ ለተጠየቀለት ምርት ወይም አገልግሎት እንደሚከ ወን የተገመተ የሽያጭ መጠን/መለኪያ  ብዛት/ እ  ጠቅላላ ዋጋ፤

5. በፕሮሞሽን ውድድሩ ሊሰጡ የተዘጋጁ ከከፍተኛው እስከ መጨረሻው ያሉ ሽልማቶችን ዝርዝር፤ለሽልማት የተዘጋጁትን ዕቃዎች መለያ ስም /ብራንድ/፤ ዕቃው የተመረተበትን አገር ፣የሽልማቱን ብዛት፣ የእያንዳንዱን ዕቃ ዋጋ በእያንዳንዱ ሽልማት ላይ ለመንግስት የሚከፈል የገቢ ግብር በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት እና ለሽልማት የተዘጋጁትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ፤

6. ዕድለኛ የሚያደርገው ዕጣ /ቆርኪ/ ከዳን የት አገር እንደሚዘጋጅ  እንደሚታተም፤ ዕድለኞች የሚታወቁት ዕጣ በማውጣት የሆነ እንደሆነ ደግሞ ዕጣው እንዴት እንደሚወጣ፤መቼ እንደሚወጣ  የፕሮሞሽን ውድድሩ ሥራ የሚካሄድበትን የጊዜ ክልል /ወሰን/፤

7. ፈቃድ ከሚጠይቅበት ዘመን በፊት ያለውን ዘመን ግብር የከፈለ ለመሆኑ  ማስረጃ ፤

8. የዘመኑን የሥራ ፈቃድ እድሳት ያደረገ ለመሆኑ ከኦርጅ ል ፈቃዱ ጋር የሚመሳከር ኮፒ ፤

9. ምርቱ ከውጭ የገባ ከሆነ ሕጋዊ በሆነ መንገድ መግባቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እ ማስታወቂያ የሚሠራለት ምርት (ሸቀጥ) ወይም አገልግሎት  ተገቢውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ ስለመሆኑ ከሚመለከተው ክፍል ማረጋገጫ፤

10. የምርቱን የመጠቀሚያ ማብቂያ ጊዜ፤ እ

11. ሌሎች ማ ቸውንም ፈቃድ ለማግኘት ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ፤

2. ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ  በፈቃድ ጠያቂው በቅድሚያ ሊታወቁ ስለሚገባቸው ግዴታዎች

ሀ. አስተዳደሩ አመልካቾች ያቀረቧቸውን መረጃዎች  ማስረጃዎች በመመርመር የተሟሉ  አሳማኝ ሆነው ሲያገኛቸው ሌሎች በአስተዳደሩ የሚፈለጉ ግዴታዎችና ክፍያዎች እንዲፈጸሙ በማድረግ ፈቃድ ይሰጣል፤

ለ. በፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅቱ ላይ ለባለዕድል የሚሰጡ ሽልማቶች በሙሉ በዓይነት ሆኖ የመጀመሪያው ሽልማት የዕቃ ዋጋ ወይም መጠንን በተመለከተ አስተዳደሩ በየበጀት ዓመት በሚወስነው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሐ. ባለዕድል የሚያደርጉ ዕጣዎች/ቶርኪ/ ክዳኖች በውጪኛው ክፍል ምንም አይነት ልዩ ምልክት ሊደረግባቸው አይገባም፤

መ. ማንኛውም ፈቃድ የሚያገኝ ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ከአስተዳደሩ ጋር ስለፕሮሞሽን ውድድሩ ዝግጅት ሁኔታ ዝግጅቱ ስለሚቆይበት ጊዜ ውል ይዋዋላል። ስለ ዕጣ ድልድሉ አፈጻጸም በውሉ ውስጥ ይመለከታል፤

ሠ. የፕሮሞሽኑ ሥራ ውጤታማ ባይሆንም ሽልማቱ ለዕድለኞች በተባለው ጊዜ መስጠት ይ ርበታል፤

ረ. ከእድለኛ የሚፈለግ የገቢግብር በፕሮሞሽን ውድድሩ አዘጋጅ አካል የሚሸፈን ይሆናል፤

ሰ. ዕድለኞች የሚታወቁት ዕጣ በማውጣት የሆነ እንደሆነ የተሸላሚዎች /የዕድለኞች/ ዝርዝር ዕጣው በወጣ በሰባት ቀ ት ውስጥ በሚዲያ መገለፅና ለአስተዳደሩ ሪፖርት ማቅረብ ይ ርበታል፤

ሸ. በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ ሰ መሠረት ተለይተው የሚታወቁ ተሸላሚዎች/እድለኞች/ዕጣው ከወጣበት እስከ 6 ወር ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሽልማቱን የማግኘት መብት ይ ራቸዋል፤

ቀ. የአንድ ዙር የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት የጊዜ ገደብ የፕሮሞሽን ውድድር እንደሚሸፍነው አካባቢና ሊሰራጭ ወይም ሊሰጥ በታሰበው የምርት ዓይነት ወይም አገልግሎት የሚወሰን ቢሆንም የጊዜው ገደቡ ከ3 ወር መብለጥ የለበትም፤

በ. የሽልማቱ አሸ ፊ /ዕድለኛ/ በምርቱ ላይ ወይም በምርቱ ክዳን ውስጥ በታተመ ምልክት የሚታወቅ የሆነ እንደሆነ አሸ ፊው ሽልማቱን የሚያገኘው በዕለቱ ወይም ለፕሮሞሽን ውድድሩ መካሄጃ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ወደ ድርጅቱ ወይም አከፋፋዬች ለቀረበው ብቻ ነው። ሆ ም ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ አሸ ፊው /ዕድለኛው/ መቅረብ ካልቻለ ዕድለኛ መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ ሰ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስተ ገድ መቻል አለበት፤

ተ. ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ አሸ ፊው የሚታወቀው በምርቱ ላይ ወይም በምርቱ ክዳን ውስጥ በታተመ ምልክት የሆነ እንደሆነ የፈቃድ ጠያቂው ሰው የምርት አከፋፋዬች ወይም ወኪሎች የአሸ ፊነቱን ማረጋገጫ ይዞ ለቀረበ ባለዕድል ሽልማቱን እንዲሰጡ ማድረግ አለበት፤

ቸ. የፕሮሞሽን ውድድሩ ከተጠናቀቀ እና በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ ሸ በተገለፀው መሠረት ዕድለኞች ዕድል ያስገኘላቸውን የአይነት ሽልማት ከተቀበሉ በኋላ አስቀድሞ ከሽልማት ዕቃው ዋጋ ላይ የተቀነሰን የገቢ ግብር በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት ለገቢ ግብር ሰብሳቢ ገቢ ማድረግና ማስረጃውን ማቅረብ ይጠበቅበታል።

3 ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ

ሀ. አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ጥያቄ በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀፅ 3.2 የተገለፁት ማስረጃዎች ካልተሟሉ ፈቃድ አይሰጥም፤

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ተራ ቁጥር 1 እ 2 ሥር በተቀመጠው መሠረት ፈቃድ ጠያቂ ሰዎች በቅድሚያ የፈቃድ ክፍያ በሽልማት ጠቅላላ ዋጋ ላይ የገቢ ግብር ተጨምሮበት የ15% ኮሚሽን ክፍያ ሳይፈጽሙ የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅቱ ፈቃድ አይሰጣቸውም፤

ሐ. ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሚያካሂዳቸውን የሎተሪ አይነቶች በሚተካ መልኩ የሚዘጋጅ የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄን አስተዳደሩ አያስተ ግድም፤

መ. ለሽያጭ ማካሄጃ ማስፋፊያ የፕሮሞሽን ውድድር እንዲዘጋጅለት የተፈለገው ምርት/ ሸቀጥ:-

1. ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ተመርቶ የገባ በሀገሪቱ የልማት የንግድ ዕድገት እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ድርሻ ጉልህ አለመሆኑ የታመነበት እንደሆነ (ለምሳሌ እንደ ማስቲካ፣ ከረሜላ፣ ብስኩት የመሳሰለው) ፈቃድ አይሰጠውም፤
2. በከፊል በውጭ ሀገር ተመርቶ ለምርት ግብአትነት ጥቅም ላይ የሚውል ነገር ግን በሀገር ውስጥ የሚመረት /መመረት የሚችል/ ተመሳሳይ የምርት/የሸቀጥ ዓይነት ካለ (ለምሳሌ እህል ወይም ዱቄት አስመጥቶ የሚያስተዋውቅ ወይም ባስመጣው ዱቄት ፓስታ ብስኩት አምርቶ የሚያስተዋውቅ ከሆነ ) ፈቃድ አይሰጠውም፤

3. የሕብረተሰቡን ባሕል ሞራል የሚጎዱ የጤንነት ጠንቅ የሆኑ ምርቶች/ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች (ለምሳሌ እንደ ሲጋራ ከ15% በላይ የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች) የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት ፈቃድ አይሰጣቸውም።

4. ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

ለሽያጭ ማካሄጃነት ማስፋፊያነት የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት እንዲያካሂድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በወንጀል የሚያስጠይቁ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ የሚችል ይሆናል፡፡

ሀ. ፈቃድ የሚያሳግዱ ሁኔታዎች፣

1. ፈቃድ ወሳጁ በተሰጠው ፈቃድ ከአስተዳደሩ ጋር ከፈጸመው ውል ውጭ ሲሰራ ከተገኘ ይህንኑ እንዲያስተካክል በጹሁፍ ተገልጾለት ለማስተካከል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

2. የፕሮሞሽን ውድድር ሥራውን አካሄድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለተሰማሩ የአስተዳደሩ ኢንስፔክተሮች ማስረጃ/ መረጃ በመስጠት ለመተባበር ፍቃደኛ ካልሆነ፤

3. በፕሮሞሽን ሥራው ላይ ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ከሰጠ እግዱ እስከሚነሳ ወይም በጉዳዩ ላይ ዘላቂ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፡፡

ለ. ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች፣

1. ፈቃድ የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
2. ያለአስተዳደሩ ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠውን ፈቃድ ለሦስተኛ ወገን በማናቸውም መንገድ አሳልፎ ከሰጠ፤
3. በተሰጠው ፈቃድ መሰረት የፕሮሞሽን ውድድር ሥራውን ሳይጀምር ሁለት ወር /60 ቀናት/ ከቆየ፤

## 4. የፈቃድ የኮሚሽን ክፍያዎች

1 ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ ለተሰጠው የፈቃድ አገልግሎት የብር 400.00 /አራት መቶ/ ክፍያ ይፈጽማል።

2 ለሽያጭ ማካሄጃ ማስፋፊያ የፕሮሞሽን ውድድር እንዲዘጋጅለት ለተፈቀደው ምርት/ሸቀጥ ወይም አገልግሎት የተዘጋጀው የሽልማት ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ ተሰልቶ በአስተዳደሩ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል (ለ) መሠረት 15% /አሥራ አምስት በመቶ/ የኮሚሽን ክፍያ ለአስተዳደሩ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡ የ15% ኮሚሽን ክፍያ የሚሰላው በሽልማቱ ላይ የሚከፈለውንና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነውን የገቢ ግብር ጨምሮ ነው፡፡

## 5. ከፕሮሞሽን ውድድር አድራጊው የሚጠበቁ ሌሎች ተጨማሪ ልዩ ልዩ ግዴታዎች

1 ለሽያጭ ማካሄጃ ማስፋፊያ የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት የሚያደርገው ሰው ለኅብረተሰቡ ስለ ፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅቱ ፣ ለሽልማቱ ዓይነትና ስለዕጣ አወጣጥ ስነ ሥርዓት ዝርዝር ሁኔታዎች በተለያዩ የመገ ኛ ብዙሀን በይፋ ማሳወቅ አለበት።

2. ባለዕድል በሚያደርገው ዕጣ/ቶርኪ/ ክዳን ላይ አወዛጋቢ ሁኔታ ቢፈጠር ውዝግቡ የተከሰተው ከዕጣው /ቶርኪው/ ክዳኑ ንትመቶችና ዝግጅት ጋር በተያያዘ የሆነ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው/ድርጅት/ ለአታሚ ኩባንያው ሁኔታውን ማሳወቅና ህጋዊ መፍትሄ የመፈለግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

3. ማንኛውም የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት እንዲያደርግ የተፈቀደለት ሰው/ድርጅት/ በዝግጅቱ ሂደት ወቅት በሙሉ አስተዳደሩ ለሚመድባቸው ኢንስፔክተሮች ለቁጥጥር ክትትል ሥራ የመተባበር ግዴታ አለበት።

4. ማንኛውም ሰው በዕጣ አወጣጥ ሽልማት አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ላይ የአስተዳደሩ ተወካይ እንዲገኝ ከ3 ቀናት በፊት በፅሁፍ ጥሪ የማድረግ ግዴታ አለበት።

5. ማንኛውም ሰው ከፈቃዱ መጀመር እስከ መጠ ቀቅ ድረስ የተደረገውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት የጽሁፍ ሪፖርት ለአስተዳደሩ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

ሀ. በሽልማት የመስጫ የጊዜ ገደቡ ውስጥ የታደሉ የሽልማት ዝርዝሮችን ከነዋጋቸው (ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው ሽልማት ድረስ ያሉትን ) ፤

ለ. ከነዚህ ሽልማቶች በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት ለገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ የተደረገበት ከየተሸላሚዎች የተቀነሰ የገቢ ግብርን የሚያስረዳ ሰነድ፤

ሐ. በጊዜ ገደቡ ውስጥ ዕድለኞች ቀርበው ያልወሰዷቸውን የሽልማት ዝርዝሮች ከነዋጋቸው አመላክቶ ካላቀረበ ድጋሚ ፈቃድ ሊሰጠው አይችልም፤

6. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃድ መጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን የፈቃድ ወረቀት ለአስተዳደሩ ተመላሽ የማድረግ ግዴታ አለበት።

7. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከተሰጠው ፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ለማድረግ ሲያስብ በቅድሚያ ለአስተዳደሩ አሳውቆ የአስተዳደሩን የጽሁፍ ይሁንታ የማግኘት ግዴታ አለበት፡፡

## 6. ቅጣት

ማንኛውም ሰው ያለፍቃድ የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት ካካሄደ አግባብ ያለው የፍትህ አካል የአስተዳደሩን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 መሰረት አድርጎ እንደጥፋቱ አይነት የሚወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

## 7. የመሸጋሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጡ የፕሮሞሽን ውድድር ፈቃዶች ቀደም ሲል ሲሰራበት በነበረው መመሪያ ይስተናገዳሉ፡፡

## 8. የተሻረ መመሪያ

ይህ መመሪያ ከመውጣት በፊት ሲሰራበት የቆየው የፕሮሞሽን ውድድር መመሪያ ቁጥር 42/2002 ተሽሮአል፡፡

9. <u>መመሪያው በሥራ ላይ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ ---------ቀን 2005 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር